እውነተኛ የክርስትና ሕይወት በእግዚአብሔር ፍቅርና በክርስቶስ ጸጋ በሚካሄደው በመንፈሳዊ ተጋድሎ መርሐ ግብር እንደሚገለጽ ከላይ በምዕራፍ ሦስት በቁጥር 3 በተሰጠው ርእስ ሥር ተመልክቷል፡፡ የተጋድሎውንም መርሐ ግብር በተጨባጭ ተግባራዊ ለማድረግ የምንችለውና ማድረግም የሚገባን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሰጠን መመሪያዎች ነው፡፡ የመጀመሪያው መመሪያችንም በቅድሚያ እግዚአብሔርን እንድናመሰግን ያሳስበናል፡፡ በእምነትና በምስጋና ሥራችንን ከጀመርን በእውነት መንፈሳዊ ተጋድሎአችን "በእግዚአብሔር ፍቅር" የሚካሄድ መሆኑን በዚህ እናውቃለን፡፡ ምክንያቱም ምስጋና፥ እግዚአብሔር ላደረገልን ቸርነትና ለፍቅሩም እኛ በበኩላችን የምንሰጠው የፍቅር ምላሽ የፍቅር መባዕ ነው፥ ስብሐተ ፍቁር ነው - ይህም ማለት የወዳጅ ወይም የወዳጅነት ምስጋና የፍቅር መዝሙር ነው፡፡ ምስጋናውንም ሆነ ሌላውን ነገር ሁሉ የምናደርገው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ስለሆነ ተጋድሎአችን በእውነት "በክርስቶስ ጸጋ" እንደሚፈጸም ፍሬም እንደሚያፈራ አንጠራጠርም፡፡ ምክንያቱም የምናደርገው ነገር ሁሉ በተቀደሰው ስሙ ስለሆነ ጸጋና በረከት አይለየውም፡፡ ተጋድሎአችንም "መንፈሳዊ ተጋድሎ" እንጂ ሥጋዊ ወይም ዓለማዊ ስላልሆነ "በመንፈስ ቅዱስ" ኃይልና ረድኤት እንደሚከናወን እናምናለን፡፡

እንግዲህ ከላይ በምዕራፍ ሦስት በቁጥር 3 መግቢያ እንደ ጠቀስነው በእግዚአብሔር ፍቅር፥ በክርስቶስ ጸጋና በመንፈስ ቅዱስ ሱታፌ (ኅብረት) በእነዚህ በሦስቱ የማይካሄድ ማናቸውም በጐ ሥራና አገልግሎት፥ መንፈሳዊ ተጋድሎ ሁሉ አይጠቅምም፡፡ ምክንያቱም ምግባር ያለ ሃይማኖት አይፈጸምምና ነው፡፡ ስለዚህ ነው በቅድሚያ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምነን እግዚአብሔርን እያመሰገንን ሥራችንን መጀመር እንዳለብን ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረን፡፡ ይህንንም በመንፈሳዊ ሕይወታችንና በሥራችን፥ በግልና በማኅበራዊ ኑሮአችን ውስጥ በተለየ መንገድ ተግባራዊ የምናደርገው ሐዋርያው በሰጠን መንፈሳዊ መመሪያዎች አማካይነት ነው፡፡

## *መመሪያዎቹን እንዴት እንመለከታቸዋለን?*

በጊዜያችን እየደገ በመጣው የኑሮ ተዕእኖ ሥርና እንዲሁም በሥራ ውጥረት ውስጥ ያሉ ሁሉ ከጸሎት፥ ከምስጋና ራሳቸውን የሚያገልሉበት ሁኔታ እየተፈጠረ ሄዷል፡፡ አብዛኛውም በልዩ ልዩ ምክንያት እምብዛም በሕይወታቸው ውስጥ ለጸሎት ቦታ አይሰጡትም፡፡ ስለዚህ የምስጋና ጸሎትን እንደ መመሪያ መውሰድ ያዳግታቸዋል፤ በመሠረቱ አንዳንዶቹ አስፈላጊነቱንም አያምኑበትም፡፡ ከጸሎት ይልቅ ለሌላ ነገር ቅድሚያ ስለሚሰጡ ከጸሎት ጋር ተለያይተው ቀርተዋል፡፡ ስለሆነም የጸሎት ነገር ሲነሣ ያጣጥሉታል፡፡ ይህ ጉዳይ በሠለጠነው ዓለም በይበልጥ ጉልቶ የሚታይ ነገር ሆኖአል፡፡

እኛ ግን እንደዚህ መሆን የለብንም፡፡ የአማኞች የመጀመሪያውና የመጨረሻው ትኩረታቸው ወደ እግዚአብሔር መሆን አለበት፡፡ የማያምኑትና የሚጠራጠሩት ይህን ሊያደርጉ አይችሉም፡፡ አማኞች ግን በየዕለቱ ግንኙነታቸው በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ነው፡፡ ከጸሎትም ጸሎት እግዚአብሔርን ስለሁሉ ነገር ማመስገን እጅግ ታላቅ ቁም ነገር ነው፡፡ ይህንን ለማወቅ የተፈጠርንበትን ዓላማ መመርመር ያስፈልጋል፡፡ እግዚአብሔርን ማመስገን የክርስትና ሃይማኖትን በትክክል ከመረዳት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በክብር የፈጠረንና በኋላም በበደላችን ስንወድቅ ያልተወንን፥ ገና በኃጢአት ሳለን እንዲሁ የወደደንና ያዳነን የእግዚአብሔርንና የፍቅሩን ታሪክ በትክክል ካወቅንና ካመንን የውለታውንና የስጦታውን ታላቅነት በእውነት ከተገነዘብን ምስጋናችንን ለእርሱ ከልብ [illegible]



ሲል የመድኃኒታችንን ወደ ዓለም መምጣትና ከእመቤታችንም መወለዱን እያስታወስን፦ "ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ" በማለት ከመላእክት ጋር እናመሰግነዋለን (ሉቃ.2፥13-14)፡፡ እንዲሁም ለኃጢአትና ለሞት ከተሰጠ ጉስቋላ ሰውነታችን በመስቀሉ ያዳነንን እሱን እያሰብን፦ "እኩት እግዚአብሔር በእንተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ" እያልን ምስጋናችንን አናቋርጥም (ሮሜ 7፥24-25)፡፡

እንግዲህ እግዚአብሔርን ማመስገን ማለት በጥቅሉ እርሱ ለአደረገልን ታላቅ ቸርነት በአፀፋው የሚሰጥ የቃልና የተግባር ምላሽ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በእኛ በሰዎች በኩል የምናቀርበው ምስጋና፥ እግዚአብሔር ለእኛ በቅድሚያ ላሳየው ለፍቅሩ የተሰጠ ምላሽ ስለሆነ ምስጋናችን እኛ ለእርሱ የምናሳየው የፍቅራችን መግለጫ እንደሆነ እናስተውላለን፡፡ ስለዚህ የመጀመሪያውን ትእዛዝ ፍቅረ እግዚአብሔርን በተግባር ለማዋል የምንችለው እርሱን በማክበርና በማመስገን ይሆናል፡፡ ለፍቅሩ የፍቅር ምላሽ መስጠት ስለ አለብን ለእርሱ የሚገባውን አውቀንና ፈቅደን ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ ለእርሱ የሚገባው ነገርና ለእኛም የሚገባን ሥራ ፈቃዱን ከመፈጸም ጋር የምስጋና መሥዋዕት ማቅረብ ነው፡፡

> *"እንግዲህ ዘወትር ለእግዚአብሔር የምስጋናን መሥዋዕት፥ ማለት ለስሙ የሚመሰክሩ የከንፈሮችን ፍሬ፥ በእርሱ /በክርስቶስ/ እናቅርብለት፡፡ ነገር ግን መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ፤ እንዲህ ያለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋልና" (ዕብ.13፥15-16)፡፡*

ከጥቅሱ እንደምንማረው ሁለት ዓይነት መሥዋዕቶች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ምስጋና ነው፤ ሁለተኛው ለሰዎች የሚደረግ መልካም ሥራ ነው፡፡ የመጀመሪያውን ብቻ ፈጽመን በዚሁ ብቻ ረክተንና ይበቃናል ብለን እንዳንቀር የእግዚአብሔር ቃል፦ "ነገር ግን መልካም ማድረግን . . . አትርሱ" በማለት ያስጠነቅቀናል፡፡ አንዳንዶች የሁለተኛውን ነገር የረሱ አሉና ማስታወሻው ያስፈልጋል፡፡ "መልካም ማድረግን ለሌሎች ማካፈልን" የሚለው ቃል በጠቅላላ ለሥጋዊና ለመንፈሳዊ ኑሮአችን የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ያካትታል፡፡ ለሌሎች ማካፈል ማለት ከሥጋዊ ሀብት ከጉልበት አገልግሎት፥ ከገንዘብና ንብረት ጀምሮ መንፈሳዊ ሀብትን ዕውቀትን፥ ትምህርትን፥ ምክርን፥ ሞያንና የመሳሰሉትን ነገሮች ሁሉ ለሌላቸው በአግባቡ ማካፈልንና አብሮ መጠቀምን ያመለክታል፡፡ እንግዲህ ለሰዎች የሚደረግ ሁለተኛው መሥዋዕት ይህ ነው፡፡

ከላይ በርእሱ ያስቀመጥናቸው ሁለቱ የማጠቃለያ መመሪያዎች ሁለቱንም ዓይነት መሥዋዕቶች ይጠይቁናል፡፡ የመጀመሪያው፥ የእግዚአብሔር ምስጋና ሁልጊዜ ስለሁሉ ነገር መሆኑን ስለሚያሳስበን ለምስጋናው ልዩ ቅርጽና ይዘት ይሰጠዋል፡፡ ምስጋናችን በተወሰነ ጊዜና ደስ ባለን ጊዜ ብቻ አለመሆኑንና በተለይም በኀዘንና በችግራችን ጊዜ እንደ ጻድቁ ኢዮብ በማናቸውም የኑሮ ሁኔታ ውስጥ ሆነን ማመስገን በእግዚአብሔር ፊት ደስ የሚያሰኝ መሥዋዕት ነው፡፡ እንደ ኢዮብ "እግዚአብሔር ሰጠ፥ እግዚአብሔር ነሣ፤ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን" ብሎ መናገር ታላቅ የምስጋና መሥዋዕት ነው፥ የከንፈሮች ፍሬ ማለት ይህ ነው፤ እርሱ በደረሰበት መከራ ሁሉ "በከንፈሩ አልበደለም" (ኢዮብ 1፥21፤2፥10)፡፡ "የከንፈሮች ፍሬ" የተባለው እንዲያው ለይስሙላ ከልቡና ሳይመነጭ እንዲሁ በዘልማድ የሚደረግ የከንፈር አገልግሎት ማለት ሳይሆን፥ ከሚወዳትና ከምትወደው ፈጣሪዋ ጋር በጸሎት የምትገኘው [illegible] ፍሬ የስብሐተ እግዚአብሔር አገልግሎቷን የሚያመለክት ነው፡፡ ስለዚህ "ነፍሴ ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኪ፡፡ ሃሌ ሉያ" እያልን

www.ethiopianorthodox.org

በዚሁ ጽሑፋችንን እናጠቃልላለን፡፡ በመጨረሻም ስሙን ያልገለጸው የመዝገበ ሃይማኖት ደራሲ በመጽሐፉ ፍጻሜ የጻፈውን በመጥቀስ የሚከተለውን ስብሐት እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር በመሆን እናቀርባለን፡፡

"ስብሐት ለእግዚአብሔር ወጣኒ ወፈጻሚ ከሃሊ ወገባሬ ኵሉ ሎቱ ይደሉ አኰቴት እስከ ዘመነ ዘመናት በምድር ወበ ሰማያት በባሕር ወበቀላያት ለዓለመ ዓለም አሜን፡-
ለሚችል ለሚጀምር ለሚፈጽም ቻይ ሁሉን ለፈጠረ እግዚአ ብሔር ምስጋና ይድረሰው ለእሱ ከዘመን እስከ ዘመናት በምድርም በሰማይም በባሕርም በጥልቆችም ለዘለዓለሙ ምስጋና ይገባዋል አሜን፡፡"

"እመሂ ስሕትኩ አንትሙ እለ በመንፈስ አርትዕዎ፡- የተሳሳትኩትም ቢኖር እናንተ በመንፈስ ያላችሁ አቃኑት" [102]

እነሣሥቶ ላስጀመረን፤ አስጀምሮ ላስፈጸመን ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይሁን፤ ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን፡፡[103]

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
0911860113
0111271609
D.N. Solomon Yohannes

102 መዝገበ ሃይማኖት፤ በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የድርሰት ክፍል ተዘጋጀ (1959 ዓ. ም.) ገጽ 111፡፡

103 "እግዚኦ ረሰየነ ድልዋነ ከመ ንበል በአኰቴት [illegible]"

www.ethiopianorthodox.org